# “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ”

## “ከእውነት ጋራ የሚጋጭ ነገር እየሰራን ለሞኖር አንድፈር”

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**

nigatuasteraye@gmail.com

ሚያዚያ ፳፻፮ ዓ.ም.

## ማሳሰቢያ፦

እንደሚታወቀው ከዚህ ቀደም በተከታታይ ያቀረብኳቸው ጽሁፎች፤ አንባቢ በግልጽ ወደሚያያቸው ክስተቶች ቀጥታ ዘልዬ በመግባት አይደለም። ይህም ባለመሆኑ፤ ከነገረ መለኮት ውስጥ ሳልገባ ህዝባውያን የሆኑትን ነገሮች ብቻ ባቀርብ ላንባቢ እንደሚቀል የተለያዩ ምክሮችና ሀሳቦች ከተለያያችሁ ወገኖቼ ቀርበውልኛል። እንደናንተ ሀሳብ ቢሆን ኖሮ ፤ ላንባቢ ጥልፍልፍ ከሚሆንበት ነገረ መለኮት ከመግባት ይልቅ፤ ወቅታውያን የሆኑትን ነገሮች ብቻ እንደክር በመምዘዝ ለማሳየት በቀለለኝ ነበር። ምክራችሁ ትክክል ቢሆንም፤ ለመቀበል ከዚህ በታች በገለጽኳቸው ምክንያቶች እንደምቸገር ተረዱልኝ።

፩ኛ፦ እኔ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቄስ እንጅ፤ ያስተዳደር ጥበብ ተንታኝ ወይም ጋዜጠኛ አድርጌ ራሴን አላቀረብኩም። እንድጽፍ የተገደድኩትም፤ ወያኔ እንደ አቡነ ማትያስ ባሉ ሰዎች ነገረ መለኮቱንና ባህሉን እያለበሰ በምትሀታዊ መንገድ ወቅታዊውን ጥፋት ወደ ኢትዮጵያ ህዝብ በመወንጨፉ የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና አቋም እንዳልሆነና ስህተት እንደሆነ ለይቼ ለማሳየት ነው።

፪ኛ፦ ለዚህም መሳሪያ አርጎ የሚጠቀምባቸው አስመሳይ መነኩሴዎችንና ሰባኪወችን ነው። የጥፋት ተልእኳቸውን የሚያቀርቡት በተወላገደ ነገረ መለኮት ሸፍነው ነው። አሁንም አቡነ ማትያስ በተቀደሰው በትንሳኤው አመታዊ በዓል የወያኔን እቅድ ሸፍነው ስላቀረቡት፤ እኔም አቀራረባቸው ስህተት መሆኑን ለማሳየት የነገረ መለኮት መምህር የሆነው ሊቅ ከትንሳኤው ጋራ አስተሳስሮ ያቀረባትን “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” የምትለዋን የማስጠንቀቂያ ሀረግ ለዚህች ጦማር ርእስ አድርጌያታለሁ። በምሥጢረ ትንሳኤው ወደ ዝርዝር ሀተታየ ዘልየ ከመግባቴ በፊት፤ ከዚህ በታች የማቀርባት መቅድም ያቡነ ማትያስን ባህርይ ትገልጽልኛለች ብየ ስላሰብኩ መንደርደሪያዬ አድርጌያተለሁ። ስለ ትእግስታችሁ አመሰግናለሁ።

# መቅድም

ይህችን ጦማር **“ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ”** በሚል ርእስ ለማዘጋጀት ምክንያት የሆነኝ፤ አቡነ ማትያስ የዘንድሮውን (የ ፳፻፮ ዓ.ም.) ትንሳኤን ምክንያት አድርገው ልጆቼ እያሉ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኖች ያቀረቡት መልእክት ሲሆን፤ አንብቤ የተሰማኝን ሀሳብ እንድሰጥ ጥያቄ ስለቀረበልኝ ነው። ሳነበው በቅኔ ትምህርት ቤት ሳለሁ ባካባቢው ተከስቶ የነበረውን ነገር አሰታወሰኝ።

ትዝታው ይህ ነው። በዋዛ በፈዛዛ ህይወቱን በማሳለፍ ላይ የነበረ አንድ ሰው ያባቱን መሬት ማረስ ረስቶ ያውሬ መፈንጫ እንዲሆን አደረገው። አጎቱ ታታሪ ሰራተኛ ነበሩና እሱ የረሳውን ደክመው አለሙት። ደክመው ካለሙት በኋላ፤ ይህ ቁም ነገር የለሽ ሰው “ያባቴ መሬት ይመለሰልኝ” ብሎ አጎቱን ባደባባይ ከሰሳቸው። እንዲመልሱለት የከሰሳቸው አጎቱ፤ በታታሪነታቸው በአራሽነታቸው ለምሳሌ የሚጠቀሱ፤ በዘመኑ በነበረው የእውቀት ደረጃም እጅግ የተማሩ፤ የተከበሩ ዳዊት ደጋሚ ነበሩ። ተከስሰው በቆሙበት አደባባይ ስለ ከሰሳቸው ሰው የሚከተለውን ተናገሩ።

“ያንተ ህይወት ከእርሻና ከምርት ጋራ የሚሄድ አይደለም። የምትውለው ከመሸታ ቤት ነው። የመሸታ ቤት ጓደኞችህ በመጠጥ የደነበዘ ጭንቅላት ያላቸው ናቸው። ከነሱ ተለይተህ ወቅቱን ጠብቀህ መሬቱን በሥራ ላይ ለማዋል ስሜቱም ብቃቱም የለህም። መሬቱን ጦም ብታሳድር መሳለቂያ ትሆናለህ” ብለው መከሩት። ሰነፉ ሰው “ድርሻየን መስጠት ስላልፈለክ ብቻ፤ ሰነፍ እንደሆንኩና ችሎታ እንደሌለኝ አድርገህ ስሜን ታጠፋለህ። እንዲያውም ስስታም፤ ምቀኛና ስም አጥፊ ነህ” እያለ የመከሩት አጎቱን የስስትና የምቀኝነት መንፈስ ያጠቃቸው እንደሆኑ አድርጎ ባደባባይ አቀረባቸው። እሳቸውም መለሱና “ይህ የተናገርኩት ባይፈጸም አንተ ራስህም አሁን ስናገር የምትሰሙኝ ሁላችሁ ታዘቡኝ” ብለው የከሳሻቸውን ደካማ ባህርይ በተሰበሰበው ህዝብ መካከል መስክረው፤ ከራሳቸው መሬት ጨምረው ከጠየቀው በላይ እጥፍ ሰጡት።

እንዳሉትም ሰውየው ከመሸታ ቤት ዋልጌዎች ራሱን ለይቶ፤ ወቅቱን ጠብቆ፤ አርሶና አለስልሶ ዘር ሊዘራበት፤ ምርት ሊያመርትበት አልቻለም። ከመሸታ ቤት ዋልጌዎች ጋራ ሲጃጃል የእርሻው ወቅት አለፈና መሬቱ ወደ ጫካነቱ ተመለሰ። እሳቸውም ከጠየቀው በላይ አትርፈው የሰጡትን የራሳቸው የነበረውን መሬት ብቻ ለይተው መነጠሩና ማረስ ሲጀምሩ “መሬቴን ነጠቀኝ” ብሎ እንደገና አጎቱን ባደባባይ ከሰሳቸው።

እሳቸውም ከሚያውቁት ከሚደግሙት መጽሐፍ **“ይነብብ ኃጥእ በዘያስህት ርእሶ”** የሚለውን ጠቅሰው ባደባባይ ተናገሩ። “ምን ማለተዎ ነው? ያብራሩቱ” ተባሉና ሲያብራሩ፤ “ይህ የወንድሜ ልጅ በመጀመሪያ እንዳልኩት፤ቀድሞውንም የተሳሳተ ሰው ነው። የሚውለው ከዋልጌዎች ጋር ነው። በህይወቱ እርፍ ጨብጦ አያውቅም። በተአምር አይታረስ? ቁም ነገር ኖሮ ህ ልታርሰው ቀርቶ እንዲያውም መሳቂያ ትሆናለህ ብየ ስነግረው፤ ምክሬን ሰምቶ አቅሙን ተገንዝቦ ሀሳቡን መቀየር ሲገባው፤ አልፎ ተርፎ እኔ የተናገርኩትን አስተባብሎና ዘልፎ የተናገረውን ሰምታችሁታል። ሲመክሩት ከማይሰማ ሰው ጋራ ምን አደናቆረኝ፤ ራሱ በተናገረውና በራሱ ሥራ መውደቁ አይቀር ብየ ፤ እንዲያውም የጠየቀውን ድርሻውን ብቻ ሳይሆን ከራሴ ድርሻ ክፍዬ ጨመሬ ሰጠሁት። ጨምሬ የሰጠሁትን መሬት ሊያርስ ይቅርና ፤ የከሰሰበትን ያባቱን ድርሻ ከዋልጌወች ጋራ ሲሚልግ ጫካ አደረገው። የራሱን ድርሻ ሳልነካ ጨምሬ የሰጠሁትን የራሴን መሬት አረስኩ” አሉና። ንግግራቸው በመቀጠል፤ **“ቃለ ዓመጻ ወጉኅሉት። ወቆመ በፍኖት እንተ በኩሉ ኢኮነት ሠናይተ” (መዝ ፴፭)** ብሎ ዳዊት የተናገረው በህይወቴ ይግጠመኝ! ብለው ንግግራቸውን አቆሙ።

ይህም ማለት “ካፉ የሚወጣው ማስመሰልና ሽንግልና ነው። የተሰለፈበት መስመር ትክክል አይደለም። ከጠጭወች ከዋልጌዎች ከመሸታው ቤት ማህበር ራሱን ካላገለለ በቀር መሬቱን አርሶ ሊያመርት ይቅርና፤ የዝንጅሮ፤ የጦጣ፤ የጃርትና የቀበሮ መናህሪያ በማድረግ ላካባቢ ጠንቅ መሆኑ የማይቀር ነው። ከራሴ ድርሻ ከፍየ የሰጠሁት መሬት ብቻ ሳይሆን ጌታችን **“እስመ ለዘቦ ይሁብዎ**

*ወለዘሂ አልቦ እለሂቦ የሀይደው"* እንዳለው ያባቴ ርስት የሚለውም ለኔ ሊመለስልኝ ይገባል"። ብለው በመናገራቸው በራሱ ላይ አስፈርደው ድርሻውንም አሳጥተው ባዶውን አደረጉት።

እንደዚሁ ሁሉ አቡነ ማትያስ እንኳን ለፓትርያርክነት ለጵጵስናውም የበቁ ባለመሆናቸው፤ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ይመራ በነበረው ሲኖዶስ ተገቢ በሆነ መንገድ ተወግዘው ከጵጵስናው የተገለሉ እንደነበሩ ሁሉም ያውቀዋል። አቡነ ማትያስ በመንበር ፓትርያርካችን ላይ ለመቀመጥ በእነ አቶ ስብሀት ነጋ በመዘገጃጀት ላይ በነበሩበት ወቅት፤ መወገዛቸውን በተመለከተ ተጠይቀው ለውግዘታቸው ምክንያት ነው ብለው የተናገሩት ሀሰት ቢሆንም፤ መወገዛቸው በምንም መንገድ ሊደበቅ የማይችል በይፋ የተነገረ ስለሆነ አምነዋል። ስለተወገዙበት ምክንያትና ስለ ውግዘቱ አነሳስ የተናገሩት ግን ሀሰት ነው። የተወገዙበት ምክንያት እሳቸው እንደሚሉት ደርግን በማውገዛቸው ሳይሆን፤ በብዙሀን መገናኛ እንደተገለጸው የኢየሩሳሌምን ገዳም ንብረት አጥፍተው ስለጠፉ ነው። አቡነ ያዕቆብ ዓቃቤ መንበር በነበሩ ጊዜ ተነሳ የሚሉትም በሁለት ምክንያቶች ቤተ ክርስቲያናችን የማትቀበለው ስህተት ነው።

፩ኛ፦ ዓቃቤ መንበር ሆኖ የሚሰየም ሰው ጊዜያውያን ነገሮች እንዳይቆሙ ምርጫው እስኪፈጸም ድረስ የነበረው እንዳለ እንዲካሄድ ለመጠበቅ ይሰየማል እንጅ በቋሚ ሲኖዶስ የተላለፉትን ቋሚ የሆኑትን ነገሮች ለማበጀትም ለመናድም አይደለም። ስለዚህ አቡነ ያዕቆብ አላነሱትም። ቢያነሱቱም ስህተት ነው።

፪ኛ፦ውግዘት እሳቸው እንደሚመስላቸው ጨዋታ አይደለም። በአቡነ ተክለሃይማኖት ይመራ የነበረው ሲኖዶስ ሲያወግዛቸው ምክንያቱን ግልጽ አድርጎ በማወጅ ነው። ይህም ተገቢና የቤተ ክርስቲያናችን ስርዓት ነው። ውግዘቱ መነሳት ያለበት በሁለት መንገዶች ነው። የተወገዘበት ምክንያት ስህተት መሆኑ ሲረጋገጥ፤ በስህተት ያወገዘው ክፍል በህይወት ቢኖርም ባይኖርም ተተችቶ ተወቅሶ ነው። ወይም ውግዘቱ ተገቢ ሆኖ በተአቅቦ የተሰጠው የዘመን ገደብ መጨረሱ ተገልጾ በይፋ እንደተወገዘ፤ መነሳቱም በይፋ ለህዝብ ይነገራል እንጅ፤ እንኳን ዓቃቤ መ ንበር፥ በተገቢው መንገድ ተመርጦ የተሰመም ፓትራያርክ ቢሆን ከሊቃውንት ጉባኤው ውሳኔ ውጭ፤ ከመንግሥት ወይም ከውጭ ድርጅት ጋራ እየተመሳጠረ የሚሰራ ከሆነ ግለ ሰብ ይሆናል። ስለዚህ አንደ ግለሰብ ብቻ ለተወጋዡ ግለ ሰብ በድብቅ በመንገር ውግዘት አይነሳም። በነዚህ በተዘረዘሩት ምክንያቶች አቡነ ማትያስ ስለመወገዛቸውና ስለመነሳቱ የተናገሩት ሁሉ "ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" ከሚለው መመሪያችን ጋራ የተጋጨ ነው። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ መሰረት አቡነ ማትያስ አሁንም ውጉዝ ናቸው። በመንበሩ ላይ ከመቀመጣቸው በፊት "ጭንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ" በሚል ርእስ የቀረበውን ጽሑፍ ይመልከቱ።

ስለ መገዛቸውም ራሳቸው የተናገሩትን ይመልከቱ።

> *መወገዙማ ደርግን አወገዝኹ እኔ፡፡ ደርግን ሳወግዝ የነበሩ ሰዎች እንዴት መንግሥትን ያወግዛል ብለው ፓትርያሪኩን አሳሳቱና አውግዘውኝ ነበር፡፡ በኋላ ስመጣ በስሕተት ነው ተብሎ አነሡት፡፡ የተወገዝኹት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ ነው፡፡ የተነሣው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስም ለቀው አቡነ ያዕቆብ ዐቃቤ መንበር በነበሩ ጊዜ ነው፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከመሾማቸው ጥቂት ጊዜ በፊት ነው ይኼ፡፡* (ምንጭ ሐራ ዘተዋሕዶ)

እውነተኛ ኢትዮጵዊ መንግሥት ቢኖር ኖሮ፤ በኢየሩሳሌም ገዳም ላይ በፈጸሙት የእምነት ማጉደልና ንብረት አጥፊነታቸው ተከሰው እስር ቤት በገቡ ነበር። ይሁን እንጅ በዓላማ ለሚተባበራቸው ለወያኔ መንግስት መጠቀሚያ ለመሆን ስለፈለጉ ብቃት የለዎትም እየተባሉ የአሜሪካ ዜግነታቸውን ወርውረው ያለብቃታቸው ያለሙያቸው የ ጓደኞቻቸውን ምክር ሰምተው፤ በነሱም ተገፍተው "ፓትሪያርክ ሆንኩላችሁ" አሉ። ከገቡ ወዲህ ሲያደርጉት የምናየው፤ ሲነገሩ የምንሰማው፤ በተለይ በዘንድሮው ፋሲካ ያቀረቡት ቃለ ቡራኬ ያዘለው መልእክት ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የራቀ ምትሀት መሳይ ነው። ቤተ ክርስቲያናችንን የወያኔ ጫካና መፈንጫ የሚያደርጋት ነው። ንግግራቸው የጓዶቻቸውን መንፈስ የሚያንጸባርቅ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ከሚያሰሙት ዋይታና ልቅሶ ጋራ የሚጋጭ በመሆኑ፤ "ይነብብ ኃጥእ በዘያስህት ርእሶ" የሚለው ቃል የተጠቀሰበት ሰው ትዝ አለኝ። ከወቅቱ ጋራ የተጋጨውን የአቡነ ማትያስን መልእክት ከትዝታየ ጋራ በማዛመድ፤ የራሳችሁ ግንዛቤና ትዝብት ይኖራችሁ ዘንድ ይህችን መልእክት ከዚህ በታች በደረደርኳቸው በሶስት አናቅጽ አቀረብኩላችሁ።

- ፩ኛ፦"ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ"
- ፪ኛ፦የአቡነ ማትያስ ንግር ወቅታዊ ከሆነው ህዝባዊ ሁኔታ ጋራ ተጋጨ።
- ፫ኛ፦ ካህናት የህዝቡን ወቅታዊ ችግር አጉልተን ማሳየት አለብን።

አሁን የነገረ መለኮት መምህር የሆነው ሊቅ ከትንሳኤው ጋራ አስተሳስሮ ባቀረባት "ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" በምትለው ሀረግ ወደ ዝርዝር ሀተታየ እሻገራለሁ።

## ፩ኛ፦"ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ"

ከሊቃውንቱ አንዱ ዮሐንስ የተባለው ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ ስለ የትንሳኤውን ነገር ሲናገር ይህችን "ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" የምትለዋን ሀረግ ተናገራት። ሙሉ ሀሳቡ እንደሚከተለው ነው። "... ተወክፈ ህማማተ እስከ ትንሣኤሁ ዘረሰዮ ይትወሀድ ምስሌሁ። እስከ ለዝሉፉ እንዘ ርሁቅ እም ኃጢአት ዘይደሉ ቦቱ እም አመ ፈጠሮ በውስተ ከርስ። ወእምድህረ ትንሳኤሁ ኮነ ኢሐማሜ ወኢመዋቴ ወኢማሳኔ ዲበ ኩሉ ገጻት፤ ወንህነሰ ኩልነ እለ ብነ ልብ ክርስቶሳዊ ዘበአማን "ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" (ሃይ ፺፡፴፰)" የሚል ነው።

ይህም ማለት፡- ጌታችን ኢየሰሱስ ክርስቶስ ከመለኮቱ ጋራ ባዋሀደው ሥጋችን በበረት ከተወለደባት ቅጽበት እስከ ትንሣኤው ድረስ የደረሰበት መከራ የሰው ዘር ሁሉ በተለያዩ ባህልና ልማድ በሚፈጽመው ወንጀል በሚፈረድበት በተደራረቡ የቅጣት አይነቶች ሁሉ ተቀጣ። የቅጣት አይነቶችን ከተቀበለ በኋላ፤ የተደራረበትን የቅጣቶችን ሃይላት ሰብሮ በኃይልና በስልጣን ተንሳ። ከተነሳ በኋል፤ በማንኛውም ሰባዊ ገጸባህርይ ከሚደርስበት ሰባዊ ነገር ሁሉ በላይ ወጣ፤ የማይሞት የማይታመም ዘላለማዊ ህያው ሆነ። ይህን ሁሉ ያደረገበት ዋናው ምክንያት ቅዱስ ጳውሎስ "ውእቱ በኩር ቀደመ እምኩሎሙ ምውታን። ተንስአ ከመ ይኩን ውእቱ ርእሰ ኩሉ" (ቆላ ፩፡ ፲፰—፳) እንዳለው እኛ ያዳም ልጆች የክርስቶስን ሁለንተና ተረድተን ካመን ከሱ ጋራ በጥምቀት ከተባበርን እንደሱ ሆነን እሱን መስለን እንድንነሳ ነው።" ዮሐንስ የተባለው ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ የትንሳኤውን ትምህርት ከገለጸ በኋላ "ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" በምትለው ሀረግ አንቀጹን ደመደመ።

"ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" ማለትም፦ ከጽድቅ ጋራ ከሚቃረኑ ነገሮች ፈጽመን መራቅ አለብን። ወንጌልን ተንተርሶ ህዝበ ክርስቲያኑ ያለበትን ወቅቱን የማይዳስስ ከጽድቅ ጋራ የሚጋጭ ነገር መናገር መስራት እናቁም። ከህብረተ ሰቡ ወቅታዊ ኑሮ ጋራ የሚቃረን ሀሳብ ማቅረብ ማስመሰልና ምትሀት ይሆናል።

## ምትሀት

ይህች "ምትሀት" የምትባል ቃል፤ በክርስቶስ ሰባዊነትና መለኮታዊነት ክስተት ላይ ተደጋግማ የምትጠቀስ ናት። የነገረ መለኮትን ጥልፍልፍ ይዘት ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች የክርስቶስ ሰባዊ አካል ረቅቆ ወይም ባህርዩን ቀይሮ ወደ ሰማይ ወጥቶ ባባቱ ቀኝ ነበረ። በሰማይ ያሉ መላእክትም በረቀቀ መልክ በሰማይ አይተውት ሰገዱለት" የሚሉ አሉ። ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ግን የለም። በናቱ ማህጸንና እቅፍ ሳለ ባባቱ ቀኝ ነበረ የምንለው በዓለም ሙሉ በሆነው መለኮቱ ነው። ያለወንድ ዘር ቃል በማሕጸነ ድንግል፤ ሥጋ ከሆነባት ቅጽበት ጀምሮ መለኮቱ ከትስብእቱ አልተለየም። ሆኖም በሰማይና በምድር ሙሉ ነው የምንለው በመለኮቱ ነው። በሥጋው ግን ከኢየሩሳሌም አልወጣም። ለዚህም ማስረጃ ከሚጠቀሱት አንዱ በሞተበት ሰአት ሞተ ተብሎ የታወጀው በነፍሱና በሥጋው መካከል በተፈጠረው መለያየት ነው። መለኮቱ ግን ከነፍሱም ከሥጋውም አልተለየም። የተለያዩ ነፍስና ሥጋ ብቻ ናቸው። ከዚህ አገላለጽ የራቀ ምትሀትና ውላጤ ከተባሉት ስህተቶች ውስጥ ይወድቃል።

በዚህ ግንዛቤ ምትሀት ማለት ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ: ማስመሰል: ማታለል: መዋሸት ማለት ነው። ለምሳሌ። "አስተርአየ ዘበአማን" ማለትም ክርስቶስ አምላክና ሰው ሲሆን ፈጽሞ በመሆን እንጅ በምትሀትና በማስመሰል አይደለም። "እፎኑመ ይብል ፩ዱ ከመ ክርስቶስ አስተርአየ በውስተ ዓለም አስተርዮተ ምትሀታዌ" ክርስቶስ ሰውም አምላክም ነው ስንል በማስመሰል በምትሀት ነው ለማለት እንዴት ይደፈራል? እንዲህማ አይደለም፣ አይባልምም። "ወአእመርዎ መላእክት እምሰማይ ከመ ፈጣሪሆሙ ውእቱ ሰብህዎ ወባረክዎ እንዘ ለሊሁ ጥብሉል በአጽርቅት ወስኩብ በውስተ ጎል" (፻፲፯፡ ፪—፱):: ማለትም፡- ክርስቶስ በተወለደበት ጊዜ መላእክት በጨርቅ ተጠቅልሎ በበረት ተኝቶ አወቁት ማለት፤ የተጠቀለለበት ጨርቅና የተኛበት በረት በረቀቀ መንገድ በሰማይ ወጣ ማለት አይደለም። ስለዚህ በትስብእቱና በመለኮቱ መካከል ያለውን ውህደት በተቃረነ መንገድ እንዳንወስደው ልንጠነቀቅ ይገባል። ይሉና ማህበራዊ ኑሯችንም ከማስመሰልና ከምትሀት መራቅ አለብን ብለው ሊቃውንት አስተምረውናል።

የተዋህዶው ነገረ መለኮት ለስሜታችንና ለስነ ምግባራችን መሰረት ነውና "ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" ከነገረ መለኮት ጋራ የተጋጫ ምትሀት የመሰለ ህዝባዊ ሀሳብ እንዳይኖረን ያልሆነውን እንደሆነ ያልተሰራው እንደተሰራ ያልተደረገውን እንደተደረገ አርገን ማቅረብ ጸያፍ ነው። በዚህ አመት የዘመናችን ፓትርያርክ ያቀረቡልን የትንሳዔው መልእክት ከተማርነው ጋራ ስናነጻጽረው ማስመሰምል

ስለሆነ ምትሀት ነው። ከቤተ ክርስቲያችን መፍለቅ የሌለበት ነው። ነገር ግን የወልድባ ገዳምን ለማፍረስ በግንባር ቀደምነት መሪዎች የሆኑት የአነ አቶ ስብሀት ነጋና የነ አባይ ፀሐዬ ንግግር መሆኑን ከዚህ በታች በምገልጸው ትንታኔ ለማሳየት እሞክራለሁ።

## ፪ኛ:-የአቡነ ማትያስ ንግግር ወቅታዊ የሆነውን የነ አቶ ስብሀት ነጋን ተልእኮ ያንጸባርቃል፤ ወቅታዊ የሆነውን ህዝባዊውን ሁኔታ ምትሀት ሆኖ ሸፍኗል።

በነረ መለኮት ጥናታችን ምትሀት ማለት ”ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ማስመሰል፣ ማታለል፣ መዋሸት ነው ብያለሁ ። አቡነ ማትያስ የተናገሩት ንግግር ከማስመሰል፣ ከምትሀት መሳይ ንግግር ርቀን እንድናስተምር እንድንኖር ከተሰየምን ካህናት ሊሰማ ይቅርና፤ ከማንም ሰው የማይጠበቅ ማስመሰል ምትሀት ነው። ስለዚህ በዘንድሮው ትንሳኤ ያቀረቡት የአቡነ ማትያስ ንግግር ቤተ ክርስቲያናችን ካስተማርችን ነገረ መለኮት ጋራ ተጋጨ። ተናገሩት ተብሎ ሐራ ዘተዋህዶ በተባለው ድረገጽ የቀረበውን ከዚህ በታች በዝርዝር እንመልከት።[ ሙሉውን ንግግር እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ::]

*“የሰው ልጅ ሕያው አምላክ በመልኩና በአምሳሉ የፈጠረው ፍጡር በመኾኑ ሕያውና ክቡር፣ ዘላለማዊና ብርሃናዊ፣ የማሰብ፣ የማመዛዘን፣ የመምረጥና የመወሰን ነጻነት ያለውና ከሌሎች ፍጥረታት ኹሉ የላቀ አእምሮ ያለው ልዑል ፍጡር ነው፡፡”* ይላሉ። ተደጋግሞ እንደተነገረው ተከብሮ የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ እሳቸውን በመንበሩ ላይ ያስቀመጣቸው የወያኔ ቡድን ያዋረደበት ዘመን ነው። ይህንንም እኩይ ተግባር ለማስፈጸም መሳሪያ ያደርጋቸው ዘንድ ወደ መንበረ ፓትርያርኩ መልምሎ የሰየማቸው ስለሆነ ያውቁታል ። በዚህ መንገድ እንደገቡም ዶ ክተር አረጋዊ በርሄ፤ “ከትግራይ ተወላጅ ብቻ የሆነበት ምክንያት ከሌላው ጎሳ ፓትርያርክ የሚሆን ጠፍቶ ነው? በማለት ከጠየቁ በኋላ፤ ያሳፍራል! ” ብለው ተናግረዋል። ሰሞኑን ብቻ በገጠር በከተማ ወያኔ አደረሰ እየተባለ በህዝብ መገናኛዎች የምንሰማው እሳቸው ከሚናገሩት ጋራ የተጋጨ ነው። “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” የሚለውን የቤተ ክርስቲያናችንን መመሪያ አፈረሱት።

ስለሰው ክቡርነት ተናገሩ እንዲባል ብቻ ለኛ ከመናገር ይልቅ ይህን ሁሉ ግፍ በዜጎች ላይ ለሚፈጽመው ለራሳቸው ቡድን የምታደርጉትን አቁሙ ብለው በግልጽ ሊናገሩት ይገባቸው ነበር። አሁን በህዝባችን ላይ የሚካሄደው ግፍ እንዳይከሰት በሰላም በተረጋጋና ሸፍጠኛ መሪ በማያንገላታው ህዝብ መካከል ሊነገር የሚገባውን መናገራቸው ማስመሰል (ምትሀት) አይደለም ሊል የሚደፍር ያለ አይመስለኝም።

እሳቸውን ፓትርያርክ አድርጎ የሰየመውን የወያኔ መንግስት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ መንደሬን ድንበሬን አታፍርስ! የምርጫ መብቴ አትንጠቅ በማለት የሚያሰማውን ጩኸት፤ በህገ ወጥነትና ባልታረም ባይነት እየፈረጀ፤ ታረሚ እያለ በማሰቃየት ላይ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ፤ “*ዘላለማዊና ብርሃናዊ፣ የማሰብ፣ የማመዛዘን፣ የመምረጥና የመወሰን ነጻነት ያለውና ከሌሎች ፍጥረታት ኹሉ የላቀ አእምሮ ያለው ልዑል ፍጡር ነው፡፡*” ይሉናል። ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ የላቀ ነው ብለው ያምኑበት ስለነበረው ስለ አቶ መለሰና በሱ ራእይ ስለሚመራው ቡድን ሊነግሩን ካልሆነ በቀር፤ ልጆቼ እያሉ የሚያደርጉት ንግግር በዚህ ወቅት ላይ ያለውን የኢትዮጵያን ዜጋ ያካተተ መልእክት አይደለም።

*“ በምርጫው መሠረት የሚሠራው ሥራ ኹሉ በእውነተኛው ዳኛ በእግዚአብሔር ፊት መልካም ኾኖ ከተገኘ ምስጋናን፣ መልካም ኾኖ ካልተገኘ ግን ተጠያቂነትንና ፍርድን ያስከትልበታል ማለት ነው፡፡”* ይላሉ። ይህ አባባል በአቶ ገብረ ኪዳን ደስታና ስብሀት ነጋ ኮርስ ሰልጥነው የወጡ ካህናት የሚናገሩት ነው። ተመልምለው የገቡት፤ ምርጫን እንደ አባቱ ገዳይ አርጎ በሚጠላው ባቶ ስብሀት ነጋ እንደሆነ እያወቅን፤ ምርጫ የ ምትለውን ቃል መንካታቸው “ይነብብ ኃጥእ በዘያስህት ርእሶ” እንደተባለው ራሳቸውን በራሳቸው ጠልፈው ከተዋል። ያስቀመጧቸው ሰዎች ምርጫ የሚሉት የነሱን ምልመላ እንደሆነ የታወቀ ነው። የመለመሏቸው ሰዎችም ድካምና ብርታት የሚመዝኑት በነሱ መመሪያ ብቻ መሆኑን እያወቅን “*በምርጫው መሠረት የሚሠራው ሥራ ኹሉ በእውነተኛው ዳኛ በእግዚአብሔር ፊት መልካም ኾኖ ከተገኘ ምስጋናን፣ መልካም ኾኖ ካልተገኘ ግን ተጠያቂነትንና ፍርድን ያስከትልበታል*” መለታቸው፤ “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” ከውነት ጋራ በሚቃረን ህይወት ለመኖር አንሞክር የሚለውን ማፍረሳቸውን በግልጽ ያሳያል። ስለዚህ ቃለ ቡራኬያቸው ቃለ መርገም። ንግግራቸው ማስመሰልና ምትሀት ነው።

ከወያኔ ቡድን በቀር ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው በመረረ ህይወት ውስጥ ነው። ታዲያ አቡነ ማትያስ *"ዛሬም ሕይወትን በሚሰጥ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለን ስለኾን የሕይወትን ጣዕም አሁንም ማጣጣም እንችላለን፡፡"* ሲሉ መናገራቸው፤ ኢትዮጵያን ተብትቦ ከያዘው ከራሳቸው ቡድን በቀር፤ ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር የትኛው ነው ህይወትን በማጣጣም ላይ ያለው? ከሳቸው ጀምሮ በግንባር የተሰለፈው ቡድን የኢትዮጵያ መሬት ካፈራቸው ቆሳቁስ አልፎ ተርፎ የህዝቡን ወዝ ደምና ቅልጥም እየመጠጠ፤ በገበርዲን በሱፍ በሀርና በወቅርቅ ሰውነቱን እያብለጨለጨ ኑሮን በማድለብ ህይወትን በማጣጣማ ላይ ያለ የሳቸው ቡድን ነው።

*"ሕይወት ጣዕም የሚኖረው በፍቅር ሲታጀብ ነው።"* የሚሉትስ በነ ስብሀት ነጋና የአቶ አባይ ፀሐዬ መካከል ስላለው ጠብቀኝ ልጠብቅህ ከሚባባሉት በዘመናችን ወያኔ በፈጠራቸው ድርጅቶች መካከል ስለሚታየው የመጎራረስ ፍቅር ካልሆነ በቀር፤ ዛሬ በወያኔ ዘመን በፍቅር የታጀበ ጣዕም ያለው ህይወት እንዲኖር የተፈቀደለት ማነው? በጎሳዎች መካከል በፍቅር የታጀበ ህይወት እንዲኖር ሲወራ ሲነገርና በተግባርም እንዲውል ሲሞከር የታየበት ወቅት አለ? **"ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ"** ከሚለው መመሪያችን የተጋጩ ምትህት ወይም ማስመሰል ነው።

የኢትዮጵያ ኃይል የጦር መሳሪያ ሳይሆን በልጆቿ መካከል በነበረው ፍጹም ፍቅር ነበር። ይህን የተረዳ ጣሊያና በኢትዮጵያውያን መካከል የነበረውን መተማመንና መፈቃቀር አደብዝዞ በጎሳ በቆንቋ ከፋፍሎ ኢትዮጵያዊነትን ደምስሶ ዘላለማዊ ባሪያ ለማድረግ በሞከረበት መንገድ እሳቸውን የጎለተ መንግስት ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ነው። እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ *"ፍጹም ፍቅር የዘላለማዊ ሕይወት ኃይል ነው፡፡"* እያሉ የተናገሩት ማስተዋል ለማይችል ምትህት ነው። ማስተዋል ለሚችል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግን የወያኔ መንግሥት ካስቀመጠው አስመሳይ ወይም በአቶ ስብሀት ነጋና አቦይ ጸሐይየ መሪነት ከተመለመለ ምትህታዊ መነኩሴ የሚነገር ምትህት ነው። ከዚህ ቀደም የነፋሌቅ ወጥመድ በሚል ርእስ የተጻፈውን ጦማር ያንብቡት። [ዝርዝሩን ለማንበብ ይህንን ሰንሰለት።]

*"ፍቅር ፍጹም የሚኾነው ሦስቱን አቅጣጫዎች ማእከል አድርጎ ሲገኝ ነው።"* ያሉትን ሐረግ ለመተንተን ሲሞክሩ *"ይኸውም ወደ ላይ እግዚአብሔርን በፍጹም ፍቅር መከተል ስንችል፣ ወደ ጎን በአርኣያ እግዚአብሔር የተፈጠረውን የሰው ልጅ በአጠቃላይ መውደድ ስንችል፣ ወደ ታች ደግሞ የምንኖርባትን ምድርና በውስጧ ያሉ ፍጥረታትን ስንከባከብ ነው።"* ይላሉ። ለመሆኑ በፍጹም ፍቅር የምንከተለው የትኛውን እግዚአብሔር ነው? በክርስትና እምነት የምንከተለው አምላክ እኮ ሰው በጎሳ በቋንቋ ተከፋፍሎ እንዲጎዳዳ የሚፈልግ አምላክ አይደለም? ሰውን ወደ ታች ወደ ምድር በመቅበር ዝቅዝቅ እየተመለከተ በውስጧ ያሉትን ጠቃሚ ነገሮች ለራሱ ብቻ እንዲዘርፍ ላንድ ቡድን የሚፈቅድ አምላም አይደለም።

*"ይህን ካደረግን ፍጹም ፍቅር ከእኛ አለ ማለት እንችላለን"*፤ የሚለው ንግግራቸውም፤ እግዚአብሄር ራሳቸውና ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈጽሙትን በደልና ግፍ እንደፈቀደላቸው አድርገው የተቀበሉት አስመስሏቸዋል። በመቀጠልም፤ *"እግዚአብሔር ይህን ዓይነት ፍቅር እንዲኖረን በሃይማኖት አስተምሮናል፡:"* ይላሉ። እሳቸው ሊናገሩት የሚፈልጉት በነአቶ ስብሀት ነጋና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ጅብ ለጥጃ፤ ተኩላ ለበግ፤ አንበሳ ለሚዳቋ ፤ ድመት ለአይጥ፤ ጭልፊት ለጫጭት ያላቸውን የፍቅር አይነት ካልሆነ በቀር፤ ለዘመናት ተሳስሮ የኖረውን ህዝብ እርስ በርሱ በማናከስ ላይ ሳሉ ይህን መናገራቸው **"ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ"** ከሚለው ጋራ በመጋጩት ንግግራቸው ምትህት ሆነ ።

*"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን <u>በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር ሊፈጸም ቀርቶ ሊወራ የማይገባውን ሰዶምንና ገሞራን በእሳት ያጋየ ግብረ ኃጢአት በኢትዮጵያ ምድር መሰማቱ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያውያን የሰጠውን የቅድስና ክብር የሚያሳጣ ከመኾኑም ሌላ በሀገራችን ላይ ልማትና ዕድገት ሳይኾን መቅሰፍትና ውድቀት እንዳያስከትልብን ኹሉም ኢትዮጵያዊ ይህን የሰዶም ግብረ ኃጢአት በጽናት መመከት"</u>* ይላሉ። <u>ለመሆኑ ከዚህ ቀደም በመሀል ኢትዮጵያ ታይቶና ተሰምቶ የማያውቅ የግብረ ኃጢአት አይነት በውስጥና በውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ ላይ ማሰራጨቱን የጀመረው ማነው? በቤተ ክርስቲያን ላይ ባስተዳደር እና የባእድ እምነት በመክተት ህዝቡን ባደባባይ መክሰስን የጀመረው ማነው? ተደጋግሞ የተወገዘው ማነው? በተሳሳተ እምነትስ ከንሳስ ድረስ መጥቶ የወደቀው ማነው?</u> "ልጅህ ወለደ? ተብሎ ሲጠየቅ መች ገና መነኮሰና በሚለው መረን በለቀቀ ባህል የምንኩስናን ክብር አዘቅት መክተትን የጀመረው ማነው? ይህን ሁሉ የግብረ ኃጢአት አይነት ከራሳቸው መፍለቁን እያወቁ፤ በኢትዮጵያውያን ፊት ቆመው ይህን ቃል መናገራቸው ማስመሰል ምትህት አይደለም ሊል የሚችል ማነው? <u>የአማራውን፣ የኦረሞውን፣ የጉራጌውንና የሌላውን ሁሉ ጎሳ ወጣት ለጫትና ለሌላም እንዳጋለጡት፤ የግብረ ሰዶሙንም ግብር እነሱ ካላመጡትበት በቀር፤ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በጥቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ ስለ ግብረ ሰዶም ርኩስነት ከአቡነ ማትያስና ከግብር አበሮቻቸው ይልቅ የበለጠ ያውቀዋል፤ ይጸየፈዋል።</u>

*“የልማታችን የጀርባ አጥንት ኾኖ እንደሚያገለግል ታላቅ ተስፋ የተጣለበት ታላቁ የሕዳሴ ግድብ በተያዘው ፍጥነት ሥራው ተሠርቶና ተጠናቆ የዕድገታችን ተሸካሚ ምሶሶ ኾኖ ማየት እንድንችል ኹሉም ኢትዮጵያዊ ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ቤተ ክርስቲያናችን ጥሪዋን ታስተላልፋለች፡፡”* ይላሉ። ይህ አባባላቸው ሊቃውንት አባቶቻችን ስለ ልማት ካስተማሩን ትምህርት ጋራ ተጋጨ። ያስተማሩንም አዲስ የልማት እቅድ ከመዘርጋት በፊት፣ መጀመሪያ መደረግ ያለበት **ነቢዩ ኢሳይያስ** የተናገረውን መንገድ መከተል እንደሆነ ነው። በመጽሀፈ ኢሳይያስ (ምዕ ፶፰፡ ከ ፮—፯) ተገልጾ እንደሚነበበው፣ ጤናማና ዘላቂ ልማታዊ መንገድ በመጀመሪያ “የበደል እስራት መፈታት አለበት። ህዝቡ የተጠመደበት የቀንበር ማነቆ መሰበር አለበት። ግርፋት መቆም አለበት። የተገፉ የተበደሉ የታሰሩ ነጻ መለቀቅ አለባቸው። ስደተኛው ሁሉ መሰብሰብ መነጋገር አለበት። የወያኔ ስውር አጀንዳ ጨርሶ መወገድ አለበት። ይህ ቀዳሚ ከሆነ ይላል ነቢዩ በቁጥር ፲፪ ላይ እንደተገለጸው፣ የአባይ ግድብ ብቻ አይደለም። ወያኔ ከገባ ጀምሮ የፈረሱት ሁሉ ስፍራዎች ይሰራሉ። የተናጋው የትውልዱም መሰረት ይታነጻል።” ከዚህ ጤናማና ዘላቂ ልማታዊ መንገድ እየተጋጩ፣ የልማት ምንጭ የሆነውን የህዝብ አዕምሮ እያደረቁ። የልማት የጀርባ አጥንት የሆነውን ወጣት በትምህርት በእውቀት በሞራል እንዳያድግ እያላሸቁ፣ የህዝቡን መንፈስ እየሰበሩ፣ የሀገርን ልዕልናን እያዋረዱ ስለ ህዳሴ ስለ አባይ ግድብ ማውራት **“ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ”** የሚለው የቤተ ክርስቲያችን ትእዛዝ የሚያውግዘው ነው።

የአቡነ ማትያስን ንግር፣ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ትንሳኤው ምንነት ከተናገረ በኋላ **“ለዚህም ነገር በእኔ በኃይል እንደሚሰራ እንዳሰራሩ እየተጋደልኩ እደክማለሁ”** ብሎ ከተናገረው ጋራ የሚመሳሰልና የሚቃረን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ስለተቀደሰው ሐዋርያዊው ተልእኮው ሲናገር፣ በሱ ውስጥ የሚሰራ ወይም እሱን እንደመሳሪያ የሚጠቀመው የላከው አምላክ እንደሆነና ፈቃዱንም በመጠበቅ በቅድስና በብጽእና እየታገለ ከግብ ለማድረስ መጣሩን ነው። የአቡነ ማትያ ንግግር ግን፣ **በተቃራኒው ቤተ ክርስቲያን እያፈረሰ አገር እየናደ የመጣው ወያኔ፣ የዘረጋውን እኩይ ተግባር፣ ታራሚና ህዳሴ እያለ የሚለፈልፈውን በሳቸው አንደበትና በሰጣቸው ስልጣን ጠቃሚ አድርገው ህዝብ ለማሳመን መናገራቸው በትኩረት ለማይመለከተው የሚያምታታ ነው። ለተመልካች ግን ህዝብን ለሚጎዳ ቡድን መልክተኝ መሆናቸውና ከሐዋርያዊ ተልእኮ ጋራ በመጋጨት ላይ መሆናቸውም ሊሰወርበት አይችልም። አቡነ ማትያስ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ወቅታዊ ጎጅ ብሎ የሚመሰክርበትን ወያኔን፣ ኢትዮጵያውያንን ለማረም ከላይ የመጣ የስርዓት መምምህርና ወቅታዊ ምሳሌ ነው ብለው ለማቅረብ የሚጥሩ አገልጋይ ናቸው።**

# ፫ኛ፡-ካህናት ወቅታውያን መሆን አለባቸው

*ይህን ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ልግለጸው ። ወቅት ሀሉት ተቃራንያን የሆኑ ነገሮች የምታገናኝ* **ቅጽበት ናት። ካህናት በቅጽበት ውስጥ የሚከሰቱትን ተቃራንያን ነገሮች በፍጥነት ተገንዝበው ህዝብ የሚጎዳውን ክስተት በውግዘት ፍላጻ ቆርጠው እየጣሉ፣ የሚጠቅመውን በማጎላመስ አጉልተው የማሳየት ኃላፊነት አለባቸው። በሆሳዕናዋ እለት በቀደስነው ቅዳሴ ላይ “ንኡ ትርአዩ ዘንተ ቅስፈተ እለ ትሳተፉ ህማመ ቢጽክሙ፣ ወእለ ትትዌከፉ ህማመ ፍቁራኒክሙ”( ጎር ቅዳ ገጽ ፪፻፸፫፡ቁ ፴” እያልን ድምጻችንን አሰምተን ለህዝበ ክርስቲያኑ ያነበብነውን እንደምሳሌ ብንወስደው፣ “ወገናዊ፣ ሰባዊ ፍቅርና ርህራሄ የሚሰማችሁ በወንድማችሁ ላይ የሚካሄደውን ግፉንና ግርፋቱን መከራውን ቀርባችሁ ተመልከቱ። መመልከትም ባቻም አይደለም፣ በመገላገል፣ በመናገር ርቆም ከሄድ ከተጎዳው ወገን ጎን በመሰለፍ መከራውን ተካፈሉ።” ማለት ነው። በሆሳዕናዋ እለት የምናነበው አመታዊ ልማድ እንዳይቀር ለማድረስ አይደለም። ወቅታዊውን ግፍና መከራ ተመልከቱ እያልን ተዘናግቶና ተዘልሎ የቆመውን ህዝብ ለመቀስቀስ ነው። ዛሬ በሀገራችን ገራፊዎችም ተገራፊዎች ወቅታውያን ሆነው የተከሰቱበት ዘመን ነው።**

**ታዲያ ሁሉም ወቅታውያን ከሆኑ የካህናት ሰልፍ ከየትኛው ጋር መሆን አለበት? በዚህ ወቅት ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አርጎ፣ ህዝቡን ለነጻነቱ እንዳይናገር አፍኖ የያዘ ቡድን ተከስቷል። ይህ ቡድን ድንበር እየሰበረ፣ አጥር እየጣሰ አብያተ ክርስቲያናትን እያፈራረሰ ንብረት እየዘረፈ የብልግና የወንበዴ ስራ እየፈጸመ የመጣ ሲሆን፣ ህዝቡ ከማነበት ሸክሙ ከብዶት ሲጮኽ፣ ታራሚ የሚል ቅጽል እየሰጠ በማሰር ላይ ነው። ታዲይ እንዲህ በመሰለ ዘመን “ንኡ ትርአዩ ዘንተ ቅስፈተ እለ ትሳተፉ ህማመ ቢጽክሙ ወእለ ትትዌከፉ ህማመ ፍቁራኒክሙ” የሚለውን ሳናስመሰል ሳናዛባ በመተርጎም ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ሰው ልጅ መሰቃየት ለሚጨነቁ፣ ለሰው ልጅ ክብር ለቆሙ በሩቅ ላሉ ኑ በኢትዮጵያውያን ላይ የተሰነዘረውን ጅራፍ ተመልከቱ። የህዝባችሁንም መከራ ለመሳተፍ ችላ አትበሉ እያልን የሳምራዊውን ህዝባዊ ፍቅርና ስሜት እንድንገልጽ የሚያስገድደን ነው።**

ለምሳሌ በሉቃስ ወንጌል ላይ ተመዝግበው ተደጋግመው የሚጠቀሱትን ካህኑን፣ ሌዋዊውንና ሳምራዊውን እንመልከታቸው። ሁሉም ወቅታውያን ናቸው። ግን ካህኑና ሌዋዊው በወንበዴዎች ከተጎዳው ሰው ጋራ ከመቆ ይልቅ፣ አይተው እንዳላዩ በማለፍ ከጉዳቱ ጋሩ ቆሙ ። ሳምራዊ ግን ወቅታዊ ችግር ከደረሰበት ሰው ጋራ ቆመ። “ሂድ አንተም እንደሱ አድርግ”(ሉቃ ፲፡፴፯) ብሎ ለተናገረው ልናሻሽለው ለማንችለው ለክርስቲያናዊ ዶ ክትሪን ተጠቃሽ ምሳሌ ሆነ። በዚህም ያቡነ ማትያስን አቋም ስንመዝነው፣ ኢየሱስ “ሂድ አንተም እንደሱ አድርግ” ብሎ ያዘዘውን ክርስቶሳዊውን ወቅታዊ ዶክትሪን ሰብረውታል። “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” የሚለውን የሊቁን ትእዛዝ ሰርዘውታል ። ካህኑና ሌዋዊው የተወቀሱት እኮ! ችግሩን አይተው ገለል ብለው በማለፋቸው ብቻ ነበር። አቡነ ማትያስ ግን ገለል ሊሉ ቀርቶ ከደብዳቢዎች ጋራ ተባብረው ህዝቡን በመደብደብ ላይ በመሆናቸው ይህ ወቅታዊ አቋማቸው ፣ ከካህኑና ከሌዋዊው ይልቅ የከፉ ያደርጋቸዋል።

ጸሎተ ማርያምን የሚደግሙ አይመስሉም። ጸሎተ ማርያም ደጋሚ ቢሆኑ ኖሮ፣ ሲሆን በገንዘቡ ከረዳው ከሳምራዊውም በላቀ ሁኔታ፣ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ “ወንጌል ብቻ ማካፈል ሳይሆን ህይወታችንንም ስለናንተ ለመከራ እንሰጣለን” እያሉ በገራፊዎች የወያኔ ወታደርና በህዝብ መካከል በቆሙ ነበር። ለዚያ ባይታደሉም እንደ ሌዋዊውና እንደ ካህኑ የህዝቡን ወቅታዊ ችግር እንዳላዩ መስለው ገለል ይሉ ነበር። እሳቸው ግን ከደብዳቢዎች ጋራ ተባብረው ህዝቡን በመደብደብ ላይ በመሆናቸው ከካህኑና ከሌዋዊው ይልቅ የከፉ ያደርጋቸዋል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግ ማርያምን የጠቀስኩበት ምክንያት፣ ጸሎተ ማርያም እያልን የምንደግመውን መናገር የጀመረችው፣ አምላኳ ፈጣሪዋ መድኀኒቷ ልጇ ያደረገላትን ለመግለጽ ነበር። ይሁን እንጅ፣ በወቅቱ የነበረውን ህዝባዊ ችግር ሳትናገር አላለፈችውም። የህዝብን ክብር ያዋርዱ የነበሩ የትዕቢተኞችንና የገዘወችን መዋረድ ተናገረች። የተገፉ የተዋረዱ የተራቡ በበረከቱ እንደሚጠገኑ ገለጸች (ሉቃ ፩፡፵፮-፶፭) ። በወያኔ እየተመለመሉ የተሰገሰጉት አስመሳይ ካህናትስ ተልእኳቸው ያው ወያኔያዊ ስለሆነ ዝም ቢሉ፣ እንዳላዩ ቢያልፉ የሚያስደንቅ አይሆንም።

የሚገርመውና ዘመኑን የከፋ ያደረገው፣ ሌሎች ካህናት ነን ባዮች የህዝቡን ወቅታዊ ችግር እያዩ ፖለቲካ ነው እያሉ፣ ራሳቸውን ንስሀ የገቡና ንስሀ ሰጭ ቅዱሳን ካህናት አርገው የሚቆጥሩት ናቸው። ችግሩን አላወቁም እንዳልል እየገቡ እየወጡ ያዩትን ሁሉ የወያኔን ክፋት ቁጭ ብለው ካንድ ከሁለት ሰው ጋራ የኢሳት ጋዜጠኞች ከሚያቀርቡት የከፋ አርገው ሲናገሩት ይሰማሉ። “ለምን በግልጽ አትናገሩትም? ሲባሉ “ይህማ ፖለቲካ ነው” ይላሉ። በነሱ ግምት ወቅታዊውን ህዝባዊ ችግር ባደባባይ አለመናገር፣ የወቅቱን ህዝባዊ ሁኔታ ከተናገረችው ከቅድስት ድንግል እመቤታችን በላይ የበለጡ ቅዱሳን እንደመሆን አድርገው የተረዱ ይመስላሉ። መፍቀርያነ ወያኔ ናቸው እንዳንላቸው፣ “ዘየሐሚ ቢጸ ኪያሁ ሰደኩ” ብሎ ዳዊት በተናገረው ሲለኩ መፍቀርያነ ወያኔ አይደሉም። ምክንያቱም ሰው የሆነ ሰው ወዳጁን በሌለበት አያማም። ይህ ባህርይ ሆድ ወዳጅነትን ከራስ ህሊና ጋራ መጋጨትን የሚያሳይና “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” ለሚለው ለክህነታዊ አቋም አለመታመን ነው።

በዚህ አጋጣሚ ሰሞኑን አየለ ታደሰ የተባሉ ሰው “ሮቢንሰን ክሩሶና ሕወሀት” በሚል ርእስ ያቀረቧት ጦማር ሳነብ “የሂሳብ ስሌትን በመዳሰስ የተለያዩ ወቅታውያን ሁኔታዎችን ለምሳሌ ያህል ምግብ ወደ ውጭ በመላክ ምን ጥቅም ይገኛል? ሕወሀት እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ በጎችን ፍየሎችን ከብቶችን ከያሉበት እያደነ፣ያገሪቱን ሀብት ለራሱ ፍላጎትና እርካታ የሚያውል፣ መኖሪያ ቤቶችን የገጠር ቦታወችን ፏሪዎችን እያፈናቀለ ይወስዳል። ሲያሰኘው ለባእድ በርካሽ ዋጋ ይቸበችባል በነጻም ያድላል።” ብለው የተናገሩት ከእውነተኛ ካህን የሚፈልቅ ወቅታዊ ተግሳጽና ምስክርነት ሆኖ ተሰማኝ።

አየለ ታደሰ እንዳሉት፣ የተዋጠውና የተበላው ንብረት ብቻ እንደሆነ ገልጸዋል። እኔ ግን የክርስቶስን ትንሳኤ ለመግለጽ እንደሚጠቀሱት እንደባቢሎን ሰዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ሁለንተና ው በዘንዶ ተውጧል እላለሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ ከዘንዶው ሊያመልጥ ሲሞክር በባእድ አገር አሳ ነበሪ እየተዋጠ በማለቅ ላይ ነው። ባንድ ዘመን የባቢሎን ሰዎች በሚያመልኩት ዘንዶ እየተዋጡ የማለቅ አስከፊ ሁኔታ ገጠማቸው። ይህን ወቅታዊ መከራ የተመለከተ አንድ የእግዚአብሄር ሰው ዘንዶውን አፈንድቶ የሚገል ነገር በሚዋጥ ሥጋ ጠቅልሎ አቀረበለት። ዘንዶው እንደ ቀድሞው እንደለመደው ተውጦ የሚቀር ሥጋ መስሎት ዋጠውና ፈንድቶ ሞተ ።

ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው ሊቅ ክርስቶስን ሊውጥ ቀርቦ ፈንድቶ የተሸነፈውን የሞትን መፈንዳት ለመግለጽ ከላይ የጠቀስኩትን የዘንዶውን ታሪክ ጠቀሰው። ሙሉ ንባቡ “ወበከመ ከይሲ ዘኮነ ያመልክዎ ሰብአ ባቢሎን ሶበ ውህጠ መብልአ ዘመጠዎ ሎቱ ነቢይ ተሰጥቀ እማእከሉ ከማሁ ተሠጥቀ ሞት ሶበ ውህጠ ሥጋሁ ለእግዚእ ወሶበ ውኅጠ ውእተ ሥጋ ቅዱሰ ሰጠቀ ከርሶ ለሲኦል ወተንስአ እሙታን (ሃይ ፳፯፡ ፲፰) የሚል ነው።

“የባቢሎንን ሰዎች ሲወጥ የነበረው ዘንዶ በዋጠው ነገር ተሰንጥቆ እንደሞተ። ሰውን ሁሉ ሲውጡ የነበሩ ሞትና ሲኦልም፤ መለኮት የተወሀደውን ነፍስ የተለየውን የክርስቶስን አካል እንደተራ ሥጋ ሊውጡ በሞከሩ ጊዜ ተሰነጠቁ ድል ተመቱ ተሸነፉ።” ብሎ አቀረበው። ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አበው የተጠቀሙባቸውን የትምህርት ስልቶች ሳንለቅ፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ሁለንተና በመዋጥ ላይ ያለውን ወቅታዊ ዘንዶ እኛ በዚህ ዘመን ያለን ካህናት፤ እንደ ቀደሙ አባቶቻችን ግልጽልጽ አድርገን ለህዝብ ማሳየት ብንችል፤ እንኳን ወገኖቻችንን ሌላውንም ባተረፍን ነበር።

በትንሳኤው ሌሊት “ትንሳኤከ ለእለ አመነ” እያልን የምናሸበሽበው ብቻ፤ የበዓላችንን አከባበር ወቅታዊ አያደርገውም። ይህንንማ በያመቱ ተደጋግሞ ሲሸበሸብ የሰማ ሁሉ ያሸበሽበዋል። የትንሳዔው መልእክት ከወያኔ ወጥመድ ተላቆ ከወቅቱ ህዝባዊ ችግር ጋራ ሰምና ወርቅ ሆኖ ካልቀረበ ማስመሰል ይሆናል። “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” የሚለውን የሊቁን ትእዛዝም መሰረዝ ይመስለኛል። “ሂድ አንተም እንደሱ አድርግ” ብሎ ያዘዘዘውን የርስቶስን ወቅታዊ ዶክትሪን መስበርም ይሆናል።

ከወቅታዊ ህዝባዊ ችግር ርቀን ከውጭ የምንጫነውን ድርሰት በህዝብ ላይ የምንዘራ ከሆን ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ “ዘከሩ ስህተተ ብዙኀነ ወኢአለው ሃይማኖተ ባህቲታ አላ ሠርዑ ወገብሩ ዕቅፍተ ወክህደተ በእከዮሙ ወደረሱ ድርሳናተ ሰይጣናዌ ወአኮ መንፈሰ አምላክዌ ከመ ያስህቱ ሰብአ” ሃ ም ፳፬፡፳) ብሎ በተናገረው ማስጠንቀቂያ ልንገሰጽ ይገባናል። ይህም ማለት፡- የተረሱትን የስህተት አይነቶችን እያሰቡ እያሰላሰሉ፤ የኃጢአት አይነት የሆነች አንዷት ነገር እንዳትቀራቸው እያደኑ፤ ሀሰቱን፤ ሽፍጡን፤ ማስመሰሉን፤ ዘረፋውን፤ ቅንጦቱን፤ ማታለሉንና ዝሙቱን እየፈለጉ በመፈጸም ለህዝብ እንቅፋቶች ሆኑ” ይህም ብቻ አይደለም። “ወደረሱ ድርሳናተ ሰይጣናዌ ወአኮ መንፈሰ አምላክዌ ከመ ያስህቱ ሰብአ” ህዝብ የሚያውቀውን እውነት እየደበቁ፤ የሰይጣንን ተግባርና ባህርያ የሚያንጸባርቀውን የሚከፋፍል የሚያፈዝና የሚያደነዝዝ ምትሀት እየጻፉ በህዝቡ ላይ እየለቀቁበት ነው።” አለ። እኛም በተመሳሳይ ባህርያችን በነ ቅዱስ አትናቴዎስ እየተከሰስን ነው።

ጵጵስናው፤ ክህነቱ፤ ቅስናው፤ ሰባኪነቱ ከወያኔዎች ማህበር ራሱን አግልሎ፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምታስተምረውን ብቻ ተንተርሶ፤ ህዝባዊውን ችግር የሚዳስስ ወቅታዊ ትምህርት ለህዝብ ማቅረብ አለበት። ህዝብ እየተናደ፤ አገር እየፈረሰ፤ ወጣቱ እየታመሰ ስለ አባይ ግድብ፤ ህዳሴና ውዳሴ እያልን የምናወራ ከሆነ በመግቢያ የጠቀስኩትን አጎቱን ከሶ የወሰደውን መሬት የዝንጅሮ የጦጣ የጃርት የቀበሮ መናህሪያ በማድረግ ላካባቢ ጠንቅ እንደሆነው ሰው መሆን ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ከምታስተምረው ትምህርት ርቀን፤ በገንዘብ በጥቅም በቡድን በፖለቲካ እየተገፋን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ላጥፊወች መናህሪያ በማድረግ ለአገር ጥፋት ጠንቅነታችን በገሀድ እየታየ ነው። እንደሳምራዊው መሆን ባንታደል፤ ራሳቸውን ገለል ካደረጉ ከሌዋዊውና ከካህኑ የባስን ከህዝቡ ደብዳቢ ጋራ የምንሰለፍ ክፉዎች መሆን እጅግ መረገምና አለመታደል ነው።

በተረፈ ቅዱስ ጳውሎስ “ወተንስአ ከመ ያጽድቀነ” (ሮሜ ፬፡፳፭)” እንዳለው፤ እኛን ለማጽደቅ የተነሳው አምላካችን” “ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ” ከምትለው መመሪያችን ጋራ እየተጋጨን ከምንኖርበት መስመር ያውጣን። ይቆየን።

ይቆየን።

**ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::**

http://www.medhanialemeotcks.org/